የሠ/መ/ቁጥር 192951

ታህሳስ 28 ቀን 2013 ዓ/ም

**ዳኞች ፡-ብርሃኑ አመነዉ**

**ተሾመ ሽፈራዉ**

**ሀብታሙ እርቅይሁን**

**ብርሃኑ መንግሥቱ**

**ነጻነት ተገኝ**

**አመልካች ፡- የኦሮሚያ የመጠጥ ዉሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ኢንተርፕራይዝ**

**ተጠሪዎች ፡-**

1. **በንቲ እምሩ**
2. **በንቲ ኢተፋ**
3. **አሰበ ተመስገን**
4. **ክፍሉ ዘዉዴ**
5. **ጉዴታ ጀቤሳ**
6. **ማሞ ኩመራ**
7. **አዱኛ ኩመራ**
8. **ምስጋናዉ ወዳጆ**
9. **ፍቃዱ አወቀ**
10. **ባጫ አልጂራ**
11. **አብዲሳ አዲሱ**
12. **ገረመዉ ሞሲሳ**
13. **አዳነ ታደሰ**
14. **ደበላ ቀጄላ**
15. **ነገራ አኤራ**
16. **ተፈራ ተኤራ**
17. **ታመነ ኢታና**
18. **ተስፋ ዲቢሳ**
19. **በላይ ሁንደራ**

**ባንቲ እምሩ፣ ተወካዮች ባንቲ ኢተፋ እና አሰበ ተመስገን ቀረቡ**

**መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡**

## ፍ ር ድ

**ጉዳዩ የሥራ ክርክር የሚመለከት ሆኖ ክርክሩ በተጀመረበት በኦሮሚያ ክልል ጊምቢ ወረዳ ፍርድ ቤት ተጠሪዎች ከሳሾች አመልካች ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ ከክርክሩ እንደተረዳነዉ ተጠሪዎች በአመልካች ላይ በቀን 17/03/2011ዓ/ም ጽፈዉ በመሰረቱት ክስ በአመልካች ድርጅት በጥበቃ ሠራተኛነት ከ2002 ዓ/ም ጀምሮ ተቀጥረዉ እየሰሩ እንደሚገኙና አመልካች ከተቀጠሩበት ጊዜ ጀምሮ ከ2008- 2010ዓ/ም ድረስ ያለዉን የሦስት ዓመት የጥበቃ ደንብ ልብስ ሰጥቷቸዉ የ6 ዓመት የጥበቃ ደንብ ልብስ፣ የዓመት እረፍት እና የትርፍ ሰዓት ክፍያ እንዳልሰጣቸዉ እንዲሁም የ9 ዓመት የሶፍትና ሳሙና እንዳልከፈላቸዉ በመግለጽ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 79/5፣ 75፣ 68(1/መ)እና 67/2 መሰረት ለእያንዳንዳቸዉ ብር 81,422.00 በድምሩ ብር 1,547,027.50 አመልካች እንዲከፍላቸዉ እንዲወሰንላቸዉ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡**

**አመልካች ለክሱ በሰጠዉ መልስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በማቅረብ ተጠሪዎች ከአመልካች ጋር ያላቸዉ ግንኙነት በቅጥር ላይ የተመሰረተ በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 162/1 ስር ከቅጥር ዉል የሚመነጭ ማንኛዉም የክፍያ ጥያቄ በ1 ዓመት ዉስጥ ካልተጠየቀ በይርጋ እንደሚታገድ እንዲሁም በአንቀጽ 162/3 መሰረት**

የትርፍ ሰዓት ክፍያ እና የመሳሰሉት ክፍያዎች በ6 ወር ጊዜ ዉስጥ ካልተጠየቀ በይርጋ እንደሚታገድ የተደነገገ በመሆኑ ተጠሪዎች የተለያዩ ክፍያ ጥያቄዎችን ያቀረቡት ከ9 ዓመት በኋላ ስለሆነ ክሳቸዉ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 162(1 እና 3) መሰረት በይርጋ የታገደ ነዉ ተብሎ ዉድቅ እንዲደረግ በመጠየቅ ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ሥልጣን ያየዉ የጊምቢ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 26215 ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ በቀን 12/11/2011 ዓ/ም በሰጠው ብይን ተጠሪዎች እንዲከፈላቸዉ የጠየቁት ከ2002 ዓ/ም እስከ 2007 ዓ/ም ድረስ አልተከፈለንም ያሉትን የተለያዩ ክፍያዎችን በመሆኑ እነዚህን ክፍያዎች በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 162 ስር በተደነገገዉ ጊዜ ዉስጥ ክስ በማቅረብ መጠየቅ ሲገባቸዉ ከረጅም ዓመት በኋላ ስለጠየቁ ክሳቸዉ በይርጋ የታገደ ነዉ በማለት ዉድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ተጠሪዎች በዚህ ብይን ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለምዕራብ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ፍርድ ቤቱ በመ/ቁጥር 42884 ላይ በቀን 01/03/2012 ዓ/ም በሰጠዉ ትእዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 337 መሰረት ሰርዞባቸዋል፡፡

በመቀጠልም ተጠሪዎች ይግባኝ ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበዉ ፍርድ ቤቱ እያመላለሳቸዉ ቆይቶ ጉዳዩን በይግባኝ የማየት ስልጣን እንደሌለዉ በመግለጽ እንዳልተቀበላቸዉ አመላክተዉ በዚህ ምክንያት አቤቱታቸዉን በሕግ በተመለከተዉ ጊዜ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ ማቅረብ እንዳልቻሉ ገልጸዉ ጊዜ ያለፈበትን ይግባኝ ማቅረብ እንዲችሉ እንዲፈቀድላቸዉ አመልክተዋል፡፡ ችሎቱም በመ/ቁጥር 320815 ላይ አመልካች መልስ እንዲሰጥ አድርጎ በቀን 24/06/2012 ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ፍርድ ቤቶችን ስልጣን እና ሥራ በድጋሚ ለመወሰን በወጣዉ አዋጅ ቁጥር 216/2011 አንቀጽ 25(2/ሀ) መሰረት የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በክልል ጉዳይ ላይ የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሰጠዉ ዉሳኔ ላይ የቀረበዉን የይግባኝ ቅሬታ ሰምቶ የመጨረሻ ዉሳኔ ለመስጠት ስልጣን አለዉ፡፡ ይህ አዋጅ በክልሉ ጋዜጣ የታተመዉ ጥር 02 ቀን 2011 ቢሆንም በአዋጁ አንቀጽ 49/2 መሰረት አዋጁ ስራ ላይ የሚዉለዉ ከ6 ወር ዝግጅት ጊዜ በኋላ እንደመሆኑ ከሐምሌ 02 ቀን 2011 ዓ/ም ጀምሮ ሥራ ላይ ዉሏል፡፡የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን በሰበር የማየት ስልጣን የሚኖረዉ በፌዴራሉ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3/ለ)፣ በኦሮሚያ ሕገ መንግስት አንቀጽ 64/4 እና በክልሉ አዋጅ ቁጥር 216/2011 አንቀጽ 25(2/ረ) መሰረት የክልል ጉዳዮች በክልሉ ፍርድ ቤቶች የመጨረሻ ዉሳኔ ሲያገኙ ነዉ፡፡በመሆኑም በተያዘዉ ጉዳይ ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 216/2011 አንቀጽ 25(2/ሀ) መሰረት ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቀርቦ ያልታየና የመጨረሻ ዉሳኔ ያላገኘ በመሆኑ ተጠሪዎች ይግባኛቸዉን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላሉ በማለት አቤቱታዉ ለሰበር ችሎቱ ብቁ እንዳልሆነ በመግለጽ ወስኗል፡፡አመልካች በቀን 28/02/2012 ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ለዚህ ችሎት ያቀረበዉም በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በተሰጠ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን የአቤቱታዉ ይዘት በአጭሩ የሚከተለዉ ነዉ፡፡

የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በተጠሪዎች የቀረበለት አቤቱታ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 327 መሰረት የሰበር አቤቱታ መቅረቢያ ጊዜ እንዳለፈባቸዉ በመግለጽ ጊዜ ያለፈበትን አቤቱታ ማቅረብ እንዲችሉ እንዲፈቀድላቸዉ በመሆኑ አቤቱታቸዉን በወቅቱ ያላቀረቡት በበቂ ምክንያት ነዉ ወይስ አይደለም የሚለዉን ብቻ መመርመር ሲገባዉ ተጠሪዎች ያልጠየቁትን ዳኝነት መርምሮ መልስ በመስጠት አመልካች ባልተከራከረበት ለዚያዉም ይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ነዉ ተብሎ በሕግ የተደነገገዉ የ30 ቀን ጊዜ ካለፈ በኋላ የቀረበዉን አቤቱታ ተቀብሎ ጉዳዩን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በይግባኝ መዳኘት አለበት ብሎ መወሰኑ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 182/2 ስር የተደነገገዉን የሚቃረን በመሆኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡እንዲሁም በክልሉ አዋጅ ቁጥር 216/2011 መሰረት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉዳዩን በይግባኝ የመመልከት ስልጣን ቢኖረዉም ይህ አዋጅ አዋጁ ከመታወጁ በፊት የተጀመሩ ጉዳዮች በቀድሞዉ አዋጅ መሰረት እልባት እንደሚያገኙ በአንቀጽ 49/1 ስር በደነገገዉ መሰረት ተጠሪዎች ክሱን አዋጁ

ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት በቀን 17/03/2011 ዓ/ም ስላቀረቡ አዋጁ ለዚህ ጉዳይ ተፈጻሚነት ስለሌለዉ ከዚህም አንጻር ዉሳኔዉ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ፡፡በተጨማሪም በአዋጅ ቁጥር 377/1996 እና በተሻሻለዉ የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 138/3 መሰረት በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ዉሳኔ ላይ ይግባኝ መቅረብ ያለበት አንድ ጊዜ ብቻ እንደሆነና በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የሚሰጠዉ ዉሳኔ የመጨረሻ እንደሆነ ተደንግጎ እያለ ለጉዳዩ አግባብነት የሌለዉን አዋጅ ቁጥር 216/2011ን በመጥቀስ ለሁለተኛ ጊዜ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉዳዩን በይግባኝ መመልከት አለበት ብሎ መወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ስለሆነ እንዲሻርልን በማለት ጠይቋል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን መርምሮ ክርክሩ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይን የሚመለከት ሆኖ እያለ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በይግባኝ መታየት አለበት ብሎ የወሰነበትን አግባብ ከአዋጅ ቁጥር 377/1996 እና ከአዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንጻር እንዲጣራ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይና ተጠሪዎች መልስ እንዲያቀቡ በማዘዙ ተጠሪዎች በቀን 13/12/2012 ዓ/ም የተጻፈ መልሳቸዉን በማቅረብ፡- ሰበር ሰሚ ችሎት በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 182/2 መሰረት የሥር ፍርድ ቤት አስተያየት ወይም ዉሳኔ መስጠት ይገባዉ ነበር ብሎ በሚገምተዉ ጉዳይ ላይ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ትእዛዝ ወይም ዉሳኔ መስጠት ስለሚችል አመልካች ባልተጠየቀ ዳኝነት ላይ ዉሳኔ ተሰጠ በሚል ያቀረበዉ አቤቱታ ተቀባይነት ሊኖረዉ አይገባም፡፡ጊዜዉ ያለፈብን በአካባዉ በተፈጠረ የጸጥታ ችግር ምክንያት እና ፍርድ ቤቶች በተለያዩ ምክንያቶች ስልጣን የለንም በሚል ሲያመላልሱን እንደሆነ ተረጋግጦ ስለተፈቀደልን አመልካች አቤቱታ ማቅረቢያ የሆነዉ የ30 ቀን ጊዜ ካለፈ በኋላ መፈቀዱ ተገቢ እንዳልሆነ በመግለጽ ያቀረበዉ አቤቱታ የሕግ ድጋፍ የለዉም፡፡ጉዳዩም በክልሉ አዋጅ ቁጥር 216/2011 መሰረት በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በይግባኝ መታየት አለበት ተብሎ በመወሰኑ የተፈጸመ ስህተት የለም ተብሎ አቤቱታዉ ዉድቅ ይደረግልን በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም በቀን 21/01/2013 ዓ/ም የተጻፈ የመልስ መልሱን በማቅረብ ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በላይ የተመለከተዉ የግራ ቀኝ ክርክርና ጉዳዩን ባዩ ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎች ይዘት ሲሆን እኛም የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ሲል ከያዘዉ ጭብጥ አንጻር በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በተሰጠዉ ዉሳኔ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነዉም ተጠሪዎች በአመልካች ላይ በወረዳ ፍርድ ቤት የመሰረቱት ክስ አልተከፈለንም ያሉትን የጥበቃ ደንብ ልብስ፣ የዓመት እረፍት ፣ የትርፍ ሰዓት እና የሶፍትና ሳሙና ክፍያ እንዳልሰጣቸዉ በመግለጽ ፍርድ ቤቱ እንዲያስከፍልላቸዉ ዳኝነት በመጠየቅ ነዉ፡፡ክርክሩ የግል የሥራ ክርክርን የሚመለከት ጉዳይ በመሆኑ በወረዳ ፍርድ ቤት ታይቶ ዉሳኔ እንዳገኘና በይግባኝ ሰሚዉ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም በይግባኝ ታይቶ እንደተወሰነ ከግራ ቀኝ ክርክር ተረድተናል፡፡ተጠሪዎች በድጋሚ ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበዉ የነበረ ቢሆንም መዝገብ ሳይከፈት ሥልጣን የለኝም በሚል ሳይቀበላቸዉ በመቅረቱ በዚህ መካከል ተጠሪዎች አቤቱታ ማቅረቢያ ጊዜ እንዳለፈባቸዉ በመግለጽ ጊዜ ያለፈበትን አቤቱታ ማቅረብ እንዲችሉ እንዲፈቀድላቸዉ ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አመልክተዋል፡፡የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ፍርድ ቤቶችን ስልጣን እና ሥራ በድጋሚ ለመወሰን በወጣዉ አዋጅ ቁጥር 216/2011 አንቀጽ 25(2/ሀ) መሰረት ጉዳዩ በድጋሚ በይግባኝ የማየት ሥልጣን ያለዉ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ነዉ በማለት አቤቱታቸዉን ለሰበር ችሎቱ ብቁ አይደለም በማለት አለመቀበሉን የዉሳኔዉ ግልባጭ ያሳያል፡፡

እንደሚታወቀዉ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 55/3 መሰረት የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ የሚገዛ ሕግ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲወጣ ከተደረገበት ምክንያቶች መካከል ዋነኛዉ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ላይ ተዋናይ

የሆኑት የአሠሪዎችና የሠራተኞች መብቶች፣ጥቅሞች እና ግዴታዎቻቸዉን ሚዛናዊ በሆነ ሁኔታ የሚያስተዳድር ሕግ ሲኖር የኢንዱስትሪ ሠላም እንዲፈጠር በማድረግ ዘርፉ ለአገራችን ከሚስገኘዉ ሁለንተናዊ ዕድገትና ልማት አንጻር ያለዉን አገራዊ ፋይዳ በማየት በወጥነት በመላዉ አገሪቱ ተፈጻሚ የሚሆን ሕግ ማዉጣት አስፈላጊ እንደሆነ በማመን መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ በዚህ አግባብ በወጣዉ አሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 137/1 እና 138 ስር አንደተመለከተዉ የግል የሥራ ክርክር በክልል ደረጃ በመጀመሪያ ደረጃ ዳኝነት ሥልጣን የሚታየዉ በክልል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነዉ፡፡እንዲሁም በአዋጁ አንቀጽ 138/3 ላይ የግል የሥራ ክርክር በክልል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ታይቶ በተሰጠዉ ዉሳኔ ቅር የተሰኘ ወገን ዉሳኔዉ በተሰጠ በ30 ቀን ዉስጥ ይግባኙን ከክልል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ይግባኝ ለሚሰማዉ የክልል ፍርድ ቤት የሥራ ክርክር ችሎት ማቅረብ እንደሚችል ተደንግጓል፡፡ ጉዳዩ ከፌዴራል የሚመነጭ ሕግ ሆኖ እያለ አዋጁ የፍርድ ቤቶችን ሥልጣን በዚህ አግባብ የወሰነበት ምክንያት ከአሠሪና ሠራተኛ ጋር የተያያዙ ክርክሮች ለአሠሪዉም ሆነ ለሠራተኛዉ የበለጠ ተደራሽ በሚሆኑ ፍርድ ቤቶች ቢታዩ በሕጉ የታለመዉን ዓላማ በተሻለ ሁኔታ ማሳካት ይቻላል የሚል የፖሊሲ አቋም በመያዙ ነዉ፡፡ እንዲሁም በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 139/2 ስር ይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት የሚሰጠዉ ዉሳኔ የመጨረሻ እንደሆነ ተደንግጓል፡፡ ‘’የመጨረሻ ዉሳኔ’’ የሚለዉ የድንጋጌዉ ሀረግ የሚያመላክተዉም በይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት ጉዳዩ ታይቶ ከተወሰነ የዉሳኔዉ ዉጤት ቢለወጥም ባይለወጥም ዉሳኔ የተሰጠበት ጉዳይ በድጋሚ በይግባኝ ሊታይ የማይችል መሆኑን ነዉ፡፡ በመሆኑም የሥራ ክርክር የሚዳኙ ፍርድ ቤቶች የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ በመላዉ አገሪቱ በወጥነት ተፈጻሚ መሆን እንዲችል በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጁ ላይ ስለክርክር አመራር የተደነገጉትን ሥነ ሥርዓታዊ ድንጋጌዎች መከተል ይኖርባቸዋል፡፡በተለይም የክልል ፍርድ ቤቶች ከሥራ ክርክር አመራር ጋር በተያያዘ ከክልላቸዉ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በተያያዘ የወጡ ክልላዊ ሕጎች ላይ የተመለከቱትን ሥነ ሥርዓታዊ ድንጋጌዎችን ተፈጻሚ በሚያደርጉበት ጊዜ በአገሪቱ በተለያዩ ፍርድ ቤቶች የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ክርክር ባላቸዉ ዜጎች መካከል ልዩነት እንዳይፈጠርና በፌዴራል ደረጃ የአሠሪና ሠራተኛ ሕግ የወጣበት ዓላማ እንዳይሳካ የሚያደርግ አሉታዊ ዉጤት እንዳይከሰት ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

ወደ ያዝነዉ ጉዳይ ስንመለስ ተጠሪዎች ያቀረቡት የግል ሥራ ክርክር በመጀመሪያ በሰበታ ወረዳ ከተማ ፍርድ ቤት ታይቶ ከተወሰነ በኋላ በይግባኛ በፊንፊኔ ዙሪያ አሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ታይቶ ተወስኗል፡፡ይህም ክርክሩ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 138 እና 139(1/ሀ) መሰረት ታይቶ መወሰኑን የሚያሳይ ነዉ፡፡በዚህ መልኩ ይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ የሰጠዉ ዉሳኔ በአዋጁ አንቀጽ 139/2 መሰረት የመጨረሻ ዉሳኔ ሥለሆነ የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ፍርድ ቤቶችን ስልጣን እና ሥራ በድጋሚ ለመወሰን በወጣዉ አዋጅ ቁጥር 216/2011 አንቀጽ 25(2/ሀ) መሰረት በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በድጋሚ በይግባኝ ሊታይ የሚችል አይደለም፡፡የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይን የሚመለከት ክርክር ለመምራትና የፍርድ ቤቶችን ሥልጣን ለመወሰን ተፈጻሚነት ያለዉ ልዩ ሕግ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ላይ የተደነገጉት ሥነ ሥርዓታዊ ድንጋጌዎች ናቸዉ፡፡ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ከወጣበት ዓላማ አንጻር ሲታይም የክልል ጉዳዮችን በተመለከተ የክልል ፍርድ ቤቶችን ሥልጣን ለመወሰን የወጣዉ አዋጅ ቁጥር 216/2011 አንቀጽ 25(2/ሀ) ስር የተደነገገዉ ለሥራ ክርክር ተፈጻሚነት ሊኖረዉ አይገባም፡፡

በመሆኑም የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በተጠሪዎች የቀረበለትን ጉዳይ በተገቢዉ ሕግ አግባብ በመመልከት ዉሳኔ የመስጠት ሥልጣን እያለዉ ለሥራ ክርክር ተፈጻሚነት በሌለዉ አዋጅ ቁጥር 216/2011 አንቀጽ 25(2/ሀ) ስር የተደነገገዉን መሰረት በማድረግ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በድጋሚ ጉዳዩ በይግባኝ መታየት አለበት ብሎ መወሰኑ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ሕግ ላይ የታለመዉ ዓላማ ከግብ እንዳይደርስ የሚያደርግና በዚሁ ሕግ የተዘረጋዉን ሥነ ሥርዓት አለመከተል በመሆኑ ሊታረም የሚገባዉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡ስለሆነም ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ዉ ሳ ኔ

1. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 320815 ላይ በቀን 24/06/2012 ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 348/1 መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የሥራ ክርክር በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት አንድ ጊዜ ታይቶ ከተወሰነ ዉሳኔዉ የመጨረሻ ስለሚሆን የተሰጠዉ የመጨረሻ ዉሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት ተብሎ በሰበር ሰሚ ችሎት ካልታየ በስተቀር በድጋሚ በይግባኝ አይታይም ብለናል፡፡
3. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መዝገቡን አንቀሳቅሶ የተጠሪዎችን አቤቱታ መርምሮ ሕግን መሰረት ያደረገ ዉሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 341/1 መሰረት መልሰንለታል፡፡
4. ግራ ቀኝ በዚህ ችሎት ያወጡትን ወጭ የየራሳቸዉን እንዲችሉ ተወስኗል፡፡

## ት እ ዛ ዝ

1. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ይተላለፍ፡፡ግራ ቀኙ ሲጠይቁም ግልባጩ ይሰጣቸዉ፡፡፡
2. በዚህ መዝገብ ላይ የተሰጠ እግድ ካለ ተነስቷል ይጻፍ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ